# Kinijit Support Forum in Atlanta (KSF Atlanta)
## የቅንጅት ድጋፍ መድረክ በአትላንታ (ቅድመ አትላንታ)

PO Box 450411, Atlanta, GA 31145   Email: groupatlanta@gmail.com


መስከረም 18 ቀን 2000 ኢ.ም.

### ለአትላንታ የቅንጅት ደጋፊዎችና አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፣

ቀደም ሲል በመላው አለም በሚገኙ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባት ሳቢያ ከአንድ አመት በላይ በእርስ በርስ እሰጥ አገባ ጊዜ ማባከናችንን በቁጭት የምናስታውሰው ነው።

በዚህ ወቅት የቅንጅት ደጋፊዎች ነን የምንልና ሎሎችም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውን በሙሉ የፓርተው አመራር በሰከነ መልኩ ችግሩን በውይይት እንዲፈታ በመጠየቅ ፈንታ በአንዳንድ ወገኖች በኩል በተናጠል ማለትም የፓርቲውን መሪ ክቡር ኤንጂነር ሀይሉ ሻውል ያንተኙበት ህዝባዊ ስብሰባ በከተማችን ለማድረግ እየተዘጋጁ መሆናቸውን ታዝበናል። ይህንን ፈር የሳተ ድርጊት እኛ በአትላንታ የምንገኝ የቅንጅት ደጋፊዎች ዝም ብለን የምንመለከት ሆኖ አላገኘነውም።

በመሆኑም የችግሩ አረንቋ ውስጥ ገብተን ለመዳከር ሳይሆን የመፍተሄው አካል ለመሆን ከሚሰሩ ጋር የበኩላችንን ለማበርከት መደራጀት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የ«**ቅንጅት ድጋፍ መድረክ በአትላንታ**» በሚል ስያሜ የተደራጀን መሆናችንን ለአገራቸው በጎ ለሚመኙ ኢትዮጵያውን ሁሉ በደስታ እናበስራለን።

ይህንኑ ምክኒያት በማድረግ የሚከተለውን መልእክት እናስተላልፋን፣

1፤ ይህንን መድረክ የመሰረትነው ብዙዎቻችን ለረዥም ጊዜ በቅንጅት ስርም ሆነ ከዚያም በፊት በአገራችን የሚካሄደውን የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል ስናግዝ የቆየን አገር ወዳዶች ነን። ሆኖም ቀድሞ በነበረው የአትላንታ የቅን ጅት ድጋፍ ቻፕተር ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ግለሰቦች በፍፁም ወገነተኝነት ድርጅቱን በቅራኔ ውስጥ እንዲውድቅ ያደረጉ በመሆናቸው እራሳችንን ከ«አትላንታ የቅንጅት ድጋፍ ቻፕተር» አግልለናል።

2፤ ወደ አሜሪካ የመጣው የቅንጅት ልዑካን ቡድን ሊቀመንበር ኢንጅነር ሀይሉ ሻውልን ሳያካትት ወይም የሊቀመንበሩን ይሁንታ ሳያገኝ የጀመረውን የተናጠል ጉብኝት አቁሞ የተፈጠረውን አለመግባባት በመወያየት እንዲፈታ ጥሪያችንን አናቀርባለን።

3፤ ይህንን የተናጠል ህዝባዊ ስብሰባ በአትላንታ እያዘጋጀ ያለው ቡድን በአንዳንድ የብዙሀን መገናኛዎች ላይ የድርጅቱ ሊቀመንበር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የማይገኙት በህመም ምክኒያት ነው በማለት የሚሰጡት መግለጫ ሀሰት እና ህዝቡን ለመደናገር መሆኑን እየገለጽን አጠቃላይ ዝግጅቱ የድርጅቱን ሊ/መንበርና የልኡካኑን መሪ ያገለለ አካሄድ መሆኑን ህዝቡ እንዲያውቀው እንፈልጋለን።

4፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የተሰዉ ወጣቶችን፤ ጎልማሶችንና አዛውንቶችን ደም መና የሚያስቀር፤ ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያን ህዝብ ተስፋ የሚያጨልም፤ የድርጅቱ መሪዎችም የደከማችሁበትንና ትልቅ ስምና ህዝባዊ ፍቅር ያተረፉችሁበትን ድርጅት የሚያዳክም ተግባር ከቀጠለ ታሪክ ይቅር የማይለው በደል መሆኑን ደግምን ደጋግመን ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።

ቅንጅት አንድ ነው!

**የቅንጅት ድጋፍ መድረክ በአትላንታ (ቅድመ-አትላንታ)**